# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ
# አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 229/2013

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገቢ የሚመነጭበት፤ የሚጠቀምና የሚተዳደር ሥርዓት ወጥ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆንና ይህንንም የሚመራ የፋይናንስ ስርዓት ማዘርጋት በማስፈለጉ፣

ሀገራችን ያላትን ውሱን የፋይናንስ ሀብት ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ ሜሌኩ ማጠቀምን አስፈላጊነት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተምሣሌት ሆነው እንዲወጡ የሚያደርግ አሰራር ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

ይህ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አውጪው ባለስልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 229/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1. "ከፍተኛ ትምህርት ተቋም" ማለት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡

2. "የወስጥ ገቢ" ማለት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተልእኮአቸውን በማስካት ሂደት ከሚያከናውናቸው ተጓዳኝ የሆኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚሰበሰቡት የዕቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ነው፡፡

3. "መደበኛ ያልሆነ ተግባር" ማለት በመደበኛ ሁኔታ ከሚከናወን የመማር ማስተማር ተግባር፣ የማኅበረሰብና የምክር አገልግሎት፣ የጥናት እና ምርምር ሥራ ወጪ የሆነ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚከናወን ተጓዳኝ የሆነ የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

## 4. የወስጥ ገቢ ምንጮች

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

- ከማታ ትምህርት ፣ ርቀት ትምህርት፣ ከረምት ትምህርትና እና መደበኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ከማስተማር የሚገኝ ክፍያ፣
- አጫጭር ስልጠናዎች /የሙያና የክህሎት ሰርተፊኬት የሚያሰጡ ሥልጠናዎች/ ከማስጠት የሚሰበሰብ ክፍያ፣
- መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት በውል ከሚደረግ ጥናት የሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣
- ለአካባቢው ማህበረሰብ ከሚሰጥ የጤና አገልግሎት ክፍያ /ሕክምና፣ መድኃኒት ሽያጭ፣ ላቦራቶሪ ወዘተ.../
- መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ከሚሰጥ የማማከር አገልግሎት ክፍያ፣
- መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሠራተኞች ለማለየት በውክልና ከሚሰጥ ፈተናና ተጓዳኝ አገልግሎቶች የሚገኝ ክፍያ፣
- ለኮንትራክተሮችና ሌሎች ተቋማት ከሚሰጥ የአፈር፣ ብረትና ሌሎች ግብዓቶችን ጥራት ለሚረጋገጥ ከሚደረግ ናሙና ምርመራ ክፍያ፣
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ /ሠራተኛ እና ተማሪ/ ግልጋሎት የተቋቋሙ መዝናኛዎች /ካፌቴሪያ፣ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ወዘተ የሚገኝ ገቢ፤
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ከተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች (ኮሚኒቲ ት/ቤት) የሚገኝ ገቢ፤
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ግልጋሎት ከተቋቋሙ መደብሮችና መጻህፍት መሸጫ ማእከላት የሚገኝ ገቢ፤
- በዋናነት የተቋማትን አካዳሚያዊ እና የምርምር ሥራዎችን ለማተም የተቋቋመ ማተሚያ ቤት ከውጭ ተጠቃሚዎች የሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣
- ከመማር ማስተማር፣ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎት ወይም ተቋም አስተዳደር ጋር ተዛማጅ ከሆኑ ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች የሚገኝን ገቢ ያጠቃልላል፡፡

## 5. <u>የውስጥ ገቢ አስተዳደር</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ በሚከተለው አኳኋን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

### 1. <u>በበጀት ዓመቱ ቀጣይነት ከሌላቸው እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች</u>

የአንድ ጊዜ ወይም ደራሽ ከሆኑና ሊታቀዱ ከማይችሉ ሥራዎች ከሚገኝ የውስጥ ገቢ ውስጥ የእነዚህን ሥራዎች ሙሉ ወጪ ሸፍኖ የሚገኝ ተራፊ ገንዘብ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ፕሬዚዳንት ሲፈቀድ መደበኛ ላልሆኑ ተግባራት ሊውል ይችላል፡፡

2. <u>በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች አጠቃቀም</u>

ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሊታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የወስጥ ገቢ፦ -

ሀ/ የወስጥ ገቢ ማጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ ይወሰናል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል "ሀ" ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘው የገቢ ማጠን የገቢ ማስገኛ ሥራዎቹን ሙሉ ወጪ ሸፍኖ ተራፊው ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአመታዊ የበጀት ጥያቄ ጋር አቅርበው የወስጥ ገቢው በመንግስት ሲታወጅ ለፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

ሐ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተስማሚ የስራ አካባቢን ለመፍጠርና ተልዕኮአቸውን ለማስለጥ ካቋቋሟቸው እንደ መዝናኛ ማእከላት፣ የተማሪዎችና ሠራተኞች መዝናኛ ክበባት፣ ጂም፣ ሬስቶራንት፣ የኮሚዩኒቲ ት/ቤቶች ፣የመጻህፍት ማእከላት፣ የማተሚያ ቤቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ሚዲብሮች እና ተመሳሳይ ተቋማት የሚገኘው ተራፊ ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ በሚያጸድቀው መሰረት ለተቋማቱ አገልግሎት ማስጫ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ እንዲሁም ለሌሎች የሥራ አመራር ቦርዱ ለሚወስናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

3. <u>የፋይናንስ አስተዳደር</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወስጥ ገቢን ጥቅም ላይ ማዋል የሚችሉት ፀንተው የሚሠራባቸውን ሕጎችና መመሪያዎች መሠረት በሚደረግ ይሆናል፡፡

4. <u>የወስጥ ገቢን ማጠቀም የሚይቻልባቸው ሁኔታዎች</u>

ሀ/ በመንግስት ወሳኔ የተሰጠባቸው እንደየተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን ለማሳሰሉት ወጪዎች ከወስጥ ገቢ ከተመን በላይ ማጠቀም አይቻልም፡

ለ/ የወስጥ ገቢን በማጠቀም ከአገር ወስጥም ሆነ ከወጭ አገር ተሸከርካሪ መግዛት አይቻልም፡

6. <u>የደረሰኝ አጠቃቀም</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5(1) እና (2) የተዘረዘሩ የወስጥ ገቢዎችን ማሰብሰብ የሚችሉት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲያሳትሙ በሚፈቀድላቸው ገቢ ማሰብሰቢያ ደረሰኞች ብቻ ነው፡፡

7. <u>የባንክ ሂሳብ</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለወስጥ ገቢ ማሰበሰቢያ በሚቀድላቸው የባንክ ሂሣብ ብቻ ማጠቀም አለባቸው፡፡

## 8. የሂሳብ አያያዝና ኦዲት

1. ለወስጥ ገቢ ራሱን የቻለ የሂሳብ ማዘገብ መቋቋምና እያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ሂሳብ መደብ ተለይቶ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2. የወስጥ ገቢ ሂሳብ በአመቱ መጨረሻ ተዘግቶ በውጭ ኦዲተር መመርመር አለበት፡፡

3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት በደረሳቸው በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ሪፖርቱን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወስጥ ኦዲት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) በተደነገገው መሰረት የወስጥ ገቢን አጠቃቀም በተመለከተ እንደ አንድ መደበኛ አሰራር በየጊዜው ኦዲት ማድረግና አፈጻጸሙን ለተቋማቱ የበላይ ኃላፊ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## 9. የወስጥ ቁጥጥር ሥርዓት

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ ሀላፊዎች የወስጥ ገቢ አስተደደርን በተመለከተ ተገቢ የሆነ የወስጥ ቁጥጥር ስርአት የማዘርጋትና ተግባራዊነቱን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 10. ተፈፃሚ ያለመሆን

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 እና 67 መሰረት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚያቋቁሟቸው ኢንተርፕራይዞች በሚገኘው ገቢ አጠቃቀም ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 11. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 01 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሐምሌ 01 ቀን 2006 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር